# ጠቃሚ ስልክ ቁጥሮችና ድረ ገፆች

**በኣደጋ ጊዜ:** ለፖሊስ፣ ኣምቡላንስ ወይም እሳት ኣገልግሎት 999 ላይ በነፃ ደውል/ይ፤ ተርጓሚዎች ኣሉ፡፡

---

**ከፈራህ/ሽ፣ ብቸኝነት ከተሰማህ/ሽ፣ ከተጨነክ/ሽ፣ ካዘንክ/ሽ፣ ከተደናገርክ/ሽ፣ ወይም ምክር ብቻ ከፈልግክ/ሽ:** በየትኛውም ጊዜ በነፃ የህፃን መስመር 0800 1111 ላይ ደውል/ይ ወይም https://www.childline.org.uk/ን ጎብኝ/ኚ

---

**ለነፃ እገዛ፣ ምክር፣ እና በተለይ በእንክብካቤ ስራ ስላሉ ወይም ከቤት ርቀው ስለሚኖሩ ልጆች መረጃ:** ወደ "እርዳታ በእጅ" የልጆች ተወካይ የምክር መስመር 0800 528 0731 ላይ ደውል/ይ (ከጥዋቱ 9-ከስዓቱ 5 ከሰኞ እስከ ኣርብ) ወይም http://www.childrenscommissioner.gov.uk/learn-more/help-at-handን እርዳታ ጎብኝ/ኚ

---

**እንድትሰራ/ሪ እየተገደድክ/ሽ ወይም መስራት የማትፈልገውን/ጊውን እንድትሰራ/ሪ እየተደረግክ/ሽ ከሆነ፣ የምትኖርበትን/ሪበትን ቦታ ለመልቀቅ ነፃ ካልሆንክ/ሽ፣ የሆነ ሰው ኣንተን/ቺን ወይም ቤተሰብህን/ሽን እያስፈራራ ከሆነ፣ እየተጎዳህ/ሽ ከሆነ ወይም ኣንድ ሰው በሌላ በየትኛውም መንገድ እየተቆጣጠረህ/ሽ ከሆነ:** ለምክር በየትኛውም ጊዜ ወደ ዘመናዊ ባርነት እርዳታ መስመር 08000 121 700 ላይ ደውል/ይ

---

**ብቸኛ ጥገኝነት ፈላጊ ልጅ ስለመሆን ምክርና እገዛ ከፈለግክ/ሽ:** ወደ የስደተኛ ምክር ቤት የልጆች ክፍል 020 7346 1134 ላይ ደውል/ይ ወይም ለ children@refugeecouncil.org.uk ኢሜይል አድርግ/ጊ

---

**በኣቅራቢያህ/ሽ እርዳታ ለመፈለግ:** www.miclu.org/servicemap

**If you are an adult and you want to help a child who you think might have been trafficked or is in danger of exploitation, or if you would like to understand more about the asylum process, you can find useful information below:**

**NSPCC's Child Trafficking Advice Centre:**
www.nspcc.org.uk

**NSPCC have a helpline 0808 800 5000 and email too:**
www.nspcc.org.uk/preventing-abuse/child-abuse-and-neglect/child-trafficking

**Every Child Protected Against Trafficking (ECPAT):**
www.ecpat.org.uk

**Coram Children's Legal Centre – Migrant Children's Project:**
www.childrenslegalcentre.com/about-us/what-we-do/migrant-childrens-project



# ማን ማን ነው?

UK ከደረስክ/ሽ በኋላ ብዙ የተለያዩ ኣዋቂዎችን ታገኛለህ/ሽ፡፡ ግን እነርሱ ሁሉ እነማን ናቸው? ይህ የሚሰሯቸውን የተለያዩ ስራዎቻቸውን እና እንዴት ሊረዱህ/ሽ እንደሚችሉ እንድትረዳ/ጂ የሚያግዝህ/ሽ መመሪያ ነው፡፡









ይህ የእውነታ ወረቀት እንግሊዝ ለደረሱና በራሳቸው ጥገኝነት ለሚፈልጉ ልጆች የተሰራ ነው፡፡

ካልተረዳኸው/ሽው አንድ አዋቂ ሰው ይህንን ኣብሮህ/ሽ እንዲያነብ ጠይቅ/ቂ፡፡

MiCLU
Migrant & Refugee Children's Legal Unit


ለምን ይህን በራሪ
ፅሁፍ ይዘህ/ሽ
የምታገኛቸውን/ኚያቸውን
ሰዎች ማን እንደሆኑ
እንዲጠቁሙህ/ሽ
ኣታደርግም/ጊም?



# IRO (ራሱን የቻለ ገምጋሚ መኮንን) (ድምጽ ማጉያ)

## እነማን ናቸው

**IRO የኣካባቢው ባለስልጣን** በእንክብካቤያቸው ስር ስትሆን/ኚ ማድረግ ያለበትን እያደረገ መሆኑን ያረጋግጣል። IRO የማህበራዊ ኣገልግሎት ምደባህ/ሽ **ላንተ/ቺ ትክክል** መሆኑንና **ደስተኛ** መሆንህን/ሽን ያረጋግጣል። IRO ከማህበራዊ ሰራተኞች **ገለልተኛና የተለየ** ነው።

## ምን ይሰራሉ

IRO የእንክብካቤ ዕቅድህ/ሽ **ለወደፊትህ/ሽ** ትክክል መሆኑን፣ ማለት የምትፈልገውን/ገውን ሁሉም ማዳመጡንና በጥንቃቄ ማየቱን፣ እንዲሁም ሁሉም የየራሱን የዕቅድ ክፍል እንደሚጠብቅ ማረጋገጥ ኣለበት። IROህን/ሽን ቢያንስ **በየስድስት ወሩ ማግኘት** ኣለብህ/ሽ።

በእንክብካቤህ/ሽ ላይ ምንም ኣይነት ችግር ካለ፣ ማህበራዊ ሰራተኛህ/ሽ እያዳመጠህ/ሽ እንዳልሆነ ከተሰማህ/ሽ፣ ወይም **ያልተፈቱ** ምንም ኣይነት **ችግሮች** ካሉ፣ ለIROህ/ሽ መንገርህ/ሽ በጣም ኣስፈላጊ ነው።



በዚህ በራሪ ፅሁፍ ላይ ያሉት ሰዎች የተዋወቁት በምታገኛቸው/ኚያቸው ቅደም ተከተል ነው። እነርሱ ሁሉም የተለያዩ ሚናዎች ኣሏቸው ቢሆንም ግን ኣንዳንድ ጊዜ ኣንድ ኣይነት ወይም የተያያዙ ሊመስል ይችላል።

እዚህ በራሪ ፅሁፍ ውስጥ ካሉት ኣዋቂዎች መካከል ኣንዳንዶቹ እንደመደበኛ የስራቸው ኣካል ስላንተ/ቺ መረጃ ለሌሎች ባለሙያዎች ማጋራት ኣለባቸው። ይህም የሆነው ኣንተን/ቺን በደንብ ለመርዳትና ለመጠበቅ በህብረት መስራት እንዲችሉ ነው።

ኣንዳንድ ኣዋቂዎች ኣንተ/ቺ ፈቃድ ካልሰጠሃቸው/ሻቸው በስተቀር ብዙውን ጊዜ ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር መረጃ ኣያጋሩም። ባብዛኛው ላንተ/ቺ ወይም ለሌላ ሰው ከባድ ኣደጋ የሚፈጥር ካልሆነ በስተቀር እነርሱ ምን ኣይነት መረጃ ማጋራት እንደሚችሉ መምረጥ ትችላለህ/ያለሽ።

# ተርጓሚ

## እነማን ናቸው

የተርጓሚ (interpreter) ሥራ ኣንተ/ቺ የምትናገረውን/ሪውን **ቃላት ሁሉ** እንደነገርካቸው/ሻቸው **በግልፅ** ወደ እንግሊዝኛ በትክክል **መተርጎማቸውን ማረጋገጥ** እና በእንግሊዝኛ የተነገሩትን ቃላቶች በሙሉ **እንድትረዳቸው/ጂቸው** ወዳንተ/ቺ ቋንቋ መተርጎም ነው።

## ምን ይሰራሉ

ከኣዋቂዎቹ ጋር በሚደረጉት **ኣብዛኞቹ ስብሰባዎች** ኣንተን/ቺን **ለመግባባት እንዲረዳህ/ሽ ተርጓሚ** ሊኖር ይችላል እና ኣንተም/ቺም ተርጓሚ **የመጠየቅ መብት ኣለህ/ሽ**። ኣንድ ተርጓሚ ላንተ/ቺ የህግ ምክር ለመስጠት ስልጠና የለውም፣ እናም **ምን እንደምታደርግ/ጊ ወይም እንደምትናገር/ሪ ሊነግርህ/ሽ ኣይገባም።**

ተርጓሚህን/ሽን በደንብ **ካልተረዳሃው/ሽው**፣ ሁሉንም ነገረ እየተርጎመልህ/ሽ እንዳልሆነ ካሰብክ/ሽ፣ ወይም ሌላ የሚያሳስብህ/ሽ ነገር ካለ ለሆነ ሰው መንገር ኣለብህ/ሽ። ተርጓሚው በምንም ኣይነት ምክንያት ካልተመቸህ/ሽ ለሌላ ተርጓሚ **የመጠየቅ መብት** ኣለህ/ሽ።





# የኣእምሮ ሃኪም

## እነማን ናቸው

የኣእምሮ ሃኪም (therapist) (ወይም የኣዕምሮ ጤና ባለሙያ) ሰዎች **ጭንቀትን** ወይም በኣስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥ ሲሆኑ የሚኖሩ **ችግሮችን** እንዲፈቱ የሚያግዝ ሰው ነው። በህክምና፣ ሰዎች ስለራሳቸው ይማራሉ እና **ችግሮቻቸውን** የሚፈቱባቸው ወይም ራሳቸውን ወይም ሁኔታቸውን የሚቀይሩባቸው መንገዶች ያገኛሉ። ባብዛኛው የሚያዋሩት ሰው ማግኘት ብቻ ደስ ይላል።

## ምን ይሰራሉ

**ሃገርህ/ሽ** ውስጥ፣ ወደ **UK** እየመጣህ/ሽ ሳለ ወይም እዚህ ከደረስክ/ሽ በኋላ እንኳ **ያጋጠሙህ/ሽ** ነገሮች **ኣስቸጋሪ ስሜቶች** እንዲሰሙህ/ሽ ሊያደርጉ ይችላሉ። ሃዘን ሊሰማህ/ሽ ልትናደድ/ጂ ወይም **መተኛት** ሊከብድህ/ሽ ይችላል። **ልትፈራም/ሪም** ትችላለህ/ሽ። ከኣዕምሮ ሃኪም ጋር መስራት ስሜቶችህን/ሽን እንድትረዳ/ጂ እና እንዴት እንዳያጨናንቁህ/ሽ ማድረግ እንድትማር/ሪ ያግዝሃል/ሻል። ይህ በዕለት ከዕለት ህይወትህ/ሽ እና በወደፊት ህይወትህ/ሽ ላይ እንድታተኩር/ሪ ይረዳሃል/ሻል። ከተስማማህ/ሽ፣ የኣዕምሮ ሃኪምህ/ሽ **ለጥገኝነት ይገባኛል ጥያቄህ/ሽ** የሚረዳ **ማስረጃ** ሊሰጥህ/ሽ ይችላል። የኣእምሮ ሃኪም ጋር ማውራት እንደሚያስፈልግህ/ሽ ከተሰማህ/ሽ የማደጎ ተንከባካቢህን/ሽን፣ ማህበራዊ ሰራተኛህን/ሽን ወይም ጠበቃህን/ሽን ጠይቅ/ቂ።



# የስደት መኮንን

## እነማን ናቸው

የስደት መኮንን **(immigration officer) ሚና የUK የፍልሰት ህጎች መከተላቸውን** ማረጋገጥ ነው። የስደት መኮንን **ኣንዳንድ ከፖሊስ ጋር የሚመሳሰሉ ስልጣናት ኣሉት** ነገር ግን የፖሊስ አባላት አይደሉም ፤ የቤት ቢሮ **(Home Office) ለተባለው የUK መንግስት** ክፍል ይሰራሉ። ኣንተ/ቺ ጥብቅ እና ደህና መሆንህን/ሽን የማረጋገጥ ሃላፊነት ኣለባቸው።

## ምን ይሰራሉ

**UK** ስትደርስ ከጉዞህ/ሽ እስከታገግም/ሚ የስደት መኮንኑ **ደህንነቱ** የተጠበቀ ቦታ ያስቀምጥሃል/ሻል። የስደት መኮንኖቹ ማን ስለመሆንህ/ሽ እና ከየት ስለመምጣትህ/ሽ **መሰረታዊ መረጃ** ይጠይቁሃል/ሻል፣ እናም እንክብካቤ ወደ ሚሰጡህ/ሽ ማህበራዊ ኣገልግሎቶች ያስተላልፉሃል/ሻል። የጥገኝነት ይገባኛል ጥያቄህንም/ሽንም ሊመዘግቡልህ/ሽ ይችላሉ። እነዚህ የስደት መኮንኖች **UK ውስጥ መቆየት ኣለመቆየትህን/ሽን እንድትወስን/ኚ ሊጠይቁህ/ሽ ኣይገባም** ነገር ግን ኣንተ/ቺ ሁል ጊዜም ለነሱ እውነተኛ መሆን ኣለብህ/ሽ እና የምትናገረውን/ሪውን ሊፅፉት ይችላሉ።



# የተመደበ መምህር

## እነማን ናቸው

የተመደበ መምህር (designated teacher) በኣካባቢው ባለስልጣን ለሚጠበቁት ልጆች **ሃላፊነት** ያለበት ትምህርት ቤትህ/ሽ ወይም ኮሌጅህ/ሽ ውስጥ ያለ መምህር ነው። በእነርሱም ምንም ኣይነት ትምህርት ላትማር/ሪ ትችላለህ/ሽ። ስለ**ሁኔታ**ህ/ሽ ትንሽ ያውቃሉ ነገር ግን ስለቤተሰብህ/ሽ ኣመጣጥ እና ለምን እየተጠበቅህ/ሽ ስለመሆኑ ግላዊ ነገሮችን ላያውቁ ይችላሉ።

## ምን ይሰራሉ

የተመደበ መምህር ኣንተን/ቺን **እንዲያግዙህ/ሽ** እና ፍላጎቶችህን/ሽን እንዲያሟሉልህ/ሽ፣ ምን እየተማርክ/ሽ እና እንዴት እየተማርክ/ሽ እንደሆነ ላይ በደንብ እየተሳተፍክ/ሽ መሆንህን/ሽን በማረጋገጥ ትምህርት ቤትህን/ሽን ወይም ኮሌጅህን/ሽን **ይረዳል**። ትምህርት ቤትህ/ሽ ወይም ኮሌጅህ/ሽ ትምህርትህ/ሽ ላይ ተፅዕኖ ሊኖራቸው የሚችሉ ጉዳዮችን እንደተረዳቸው ያረጋግጣሉ፤ እና እንዴ**ት እየሰራህ/ሽ መሆ**ኑን ይመዘግባሉ። ለኣንተ/ቺ የግል ትምህርት ዕቅድ **(Personal Education Plan (PEP))** ሃላፊነት ይወስዳሉ።

የተመደበ መምህር ትምህርት ቤት እንዴት እየሄደልህ/ሽ መሆኑን ለማህበራዊ ሰራተኛህ/ሽ በየጊዜው ይነግረዋል። የተመደበ መምህርህ/ሽ እንደምትጠበቅ/ቂ ለሌሎች ተማሪዎች ሊናገር ወይም በነሱ ፊት በተለየ መልኩ ሊያይህ/ሽ ኣይገባም።



# ማህበራዊ ሰራተኛ

## እነማን ናቸው

ማህበራዊ ሰራተኛ (social worker) በኣካባቢው ያሉትን ልጆች የማገዝ ሃላፊነት ያለው ሰው ነው። የሚንከባከብህ/ሽ ቤተሰብ ሳይኖርህ/ሽ ብቻህን ስለሆንክ/ሽ ኣንተን/ቺን የመጠበቅ ሃላፊነት የአካባቢው ባለስልጣን ነው። የምትኖርበት/ሪበት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ፣ ምግብ፣ ልብሶች፣ የጤና ሽፋን፣ ትምህርት እና እንደ ልጅ የሚያስፈልጉህን/ሽን ሌሎች አገዛዎች እንደሚኖሩህ/ሽ ያረጋግጣሉ። ይህም ጥበቃ ማግኘት **(“looked after”)** ወይም እንክብካቤ ማግኘት **(“in care”)** ተብሎ ይጠራል።

## ምን ይሰራሉ

ማህበራዊ ሰራተኞቹ ስላንተ/ቺ እንክብካቤ ውሳኔ ይሰጣሉ። ማህበራዊ ሰራተኛህ/ሽ **ቢያንስ በየስድስት ሳምንቱ ሊጎበኙህ/ሽ** ይገባል። **ሊያዳምጡህ/ሽ** እንዲሁም **ፍላጎቶችህን/ሽን** እና **ስሜቶችህን/ሽን** በእንክብካቤህ/ሽ እቅድ ውስጥ **ሊያካትቱልህ/ሽ** ይገባል። **ውሳኔዎችን ሊያብራሩልህ/ሽ** እና ድምፅህን/ሽን እንዴት ማሰማት እንደምትችል/ይ ማወቅህን/ሽን ሊያረጋግጡ ይገባል። እንግሊዝኛ የማትረዳ/ጂ ከሆነ ሁልጊዜም ተርጓሚ በመጠቀም ሊያናግሩህ/ሽ ይገባል። ኣንዳንዴ ስለሚቀያየሩ ከኣንድ በላይ ማህበራዊ ሰራተኞች ሊኖሩህ/ሽ ይችላሉ። ምንጊዜም የማህበራዊ ሰራተኛህን/ሽን **ስም እና ቁጥር** ካንተ/ቺ ጋር አስቀምጥ/ጪ።



**ከምንም ኣይነት ኣካላዊ ጥቃት፣ ኣእምሮኣዊ ጥቃት፣ ብዝበዛ ወይም ንቀት የመጠበቅ መብት ኣለህ/ሽ።**

- የሚጎዳህ/ሽ ሰው ካለ
- ኣንድ ኣዋቂ መንከባከብ ያለበትን ያህል ካልተንከባከበህ/ሽ
- የራሱን ስራ ወይም መስራት የማትፈልገውን/ጊውን ስራ የሚያሰራህ/ሽ ከሆነ
- የምትቆይበትን ቦታ ለመልቀቅ ነፃ ካልሆንክ/ሽ*
- አንተ/ቺ ወይም ቤተሰብህ/ሽ ላይ መጥፎ ነገር ላደርግ እችላለሁ የሚልህ/ሽ ካለ
- ኣንድ ሰው ላይ የሆነ እዳ ስላለብህ/ሽ ነፃ ካልሆንክ/ሽ
- በሆነ በሌላ ምክንያት ከፈራህ/ሽ...

**...ሊረዱህ/ ሽ የሚችሉ ሰዎች ኣሉ፣ ግን ለኣንድ ሰው ማመንና መንገር ኣለብህ/ሽ። ለማህበራዊ ሰራተኛህ/ሽ፣ ለማደጎ ተንከባካቢህ/ሽ ወይም በዚህ በራሪ ፅሁፍ ውስጥ ካሉት በጣም ለሚመችህ/ሽ ማንኛውም ሰው ተናገር/ሪ፣ ወይም በዚህ በራሪ ፅሁፍ ጀርባ ላይ ካሉት ቁጥሮች ወደየትኛውም ደውል/ይ።**

*ኣንዳንድ ጊዜ UK ውስጥ የኣካባቢው ባለስልጣን ካንተ/ቺ ጋር ለመገናኘት ደህንነት የሌለው ኣዋቂ ኣለ ብሎ ካመነ፣ ደህንነትህን/ሽን ለመጠበቅ ሲባል መሄድ የምትችልበት/ይበትን ቦታና ማየት የምትችለውን/ይውን ነገር ለተወሰነ ጊዜ ሊገድበው ይችላል። ይህን ሊያብራሩልህ/ሽ ይገባል። ደስተኛ ካልሆንክ/ሽ ወይም ከተደናገርክ/ሽ ስለዚህ ነገር ከጠበቃህ/ሽ ወይም ከሌላ ሰው ጋር መነጋገር ትችላለህ/ያለሽ።



# ሁሉም ልጆች ተመሳሳይ መብቶች ኣሏቸው፡፡

- **ድምፄን የማሰማት** መብት
- **የቤት፣ ምግብና እንክብካቤ** መብት
- **ከኣካላዊ ጉዳትና በደል የመጠበቅ** መብት
- ሃኪም/የጥርስ ሃኪም የማየትና **በነፃ ህክምና** የማግኘት መብት
- **የነፃ፣ የሙሉ ጊዜ ትምህርት** መብት
- **ያለመታሰር** መብት
- **ቤተሰቦቼን የማግኘት** መብት
- **ያለመገለል** መብት
- እድሜዬ ሲጨምር **ሙሉ በሙሉ የማደግ** መብት

እውነታ: **በ UK ህግ እይታ ኣንድ ሰው እድሜው 18 እስኪሞላው ድረስ ህፃን ነው፡፡ ኣካባቢያዊ ባለስልጣኖች ቤተሰብ የሌለው ልጅ 18 እስኪሞላው፣ በኣንዳንድ ኣጋጣሚዎች ከዚያ እድሜም በኋላም የመንከባከብ ህጋዊ ግዴታ ኣለባቸው፡፡ በራሳቸው UK የደረሱ ጥገኝነት ፈላጊ ህፃናት እንክብካቤ ውስጥ የሚገቡት በዚህ ምክንያት ነው፡፡**





# የማደጎ ተንከባካቢ

## እነማን ናቸው

የማደጎ ተንከባካቢ (foster carer) ማለት **የሚጠብቃቸው ቤተሰብ የሌላቸውን ልጆች** ለመንከባከብ **ቤቱን የሚከፍት** ሰው ነው።

## ምን ይሰራሉ

የማደጎ ተንከባካቢዎች ሰላማዊና ደህንነቱ የተጠበቀ ቤት ያቀርባሉ። በየቀኑ **ይንከባከቡሃል/ሻል** ፣ ትምህርት ቤት ይወስዱሃል/ሻል እና እንደ ልባሳትና ምግብ ያሉ የሚያስፈልጉህን/ሽን ነገሮች ያቀርቡልሃል/ሻል። የማደጎ ተንከባካቢ እንደ ማህበራዊ ሰራተኛህ/ሽ **(social worker)** ፣ ጠቅላላ ሃኪምህ/ ሽ **(GP)** ፣ **ጠበቃህ/ሽ** እና **መምህሮች/ሽ** ባሉ ባንተ/ቺ ህይወት ውስጥ ከሚሳተፉ ብዙ ሳውቂዎች ጋርም ግንኙነት ይኖረዋል። የቤተሰባቸው ኑሮ ላንተ/ቺ እንደለመድከው/ሽው ላይሆን ይችላል እናም ይህ ከከበደህ/ሽ እንዲረዱህ/ሽ ስሜትህን/ሽን ማጋራት ጠቃሚ ነው።



# የፖሊስ መኮንን

## እነማን ናቸው

የፖሊስ መኮንን (police officer) የሰዎችን ደህንነት የማስጠበቅ፣ **UK** ውስጥ ህጉ መተግበሩን የማረጋገጥና ወንጀል የመመርመር ሃላፊነት ያለበት ነው። የፖሊስ መኮንኖችም ህጉን መከተል ኣለባቸው።

## ምን ይሰራሉ

ኣደጋ ውስጥ ከሆንክ/ሽ ወይም ወንጀል መዘገብ ከለግክ/ሽ በቻልከው/ሽው ፍጥነት ለፖሊስ መናገር ኣለብህ/ሽ ። 999 ደውል/ይ።

ለፖሊስ መናገር ከፈራህ/ሽ ወይም የግል መረጃህን/ሽን መስጠት ካልፈለግክ/ሽ ለሌላ የምታምነው/ኝው ኣዋቂ ተናገር/ሪ። የግል መረጃህን/ሽን ሳታቀርብ/ቢ ወንጀሎቹ ሊዘገቡ ይችላሉ።


የ **UK** የወንጀል ህግ ከሃገርህ/ሽ የወንጀል ህግ ጋር በጣም **ሊለያይ** ይችላል። ለምሳሌ ጎዳና ላይ ሲጋራ በመጣል ቅጣት ልታገኝ/ኚ ትችላለህ/ያለሽ። ህጉን የበለጠ ለመረዳት እንዲያግዙህ/ሽ ማህበራዊ ሰራተኛህን/ሽን ወይም ሌላ ኣዋቂ ጠይቅ/ቂ።

በወንጀል ከተከሰስክ/ሽ በፖሊስ መኮንን በምትጠየቅበት/ቂበት ጊዜ ጠበቃህ/ሽ ኣብሮህ/ሽ እንዲሆን የማድረግ መብት ኣለህ/ሽ።

ሌላ ሰው ወንጀል እንድትሰራ/ሪ ኣርጎህ/ሽ ከሆነ **ኣንተ/ቺ** ተጠቂ ነህ/ሽ፣ እና **ኣንተ/ቺ እርዳታ እና ጥበቃ** ያስፈልግሃል/ሻል።

ኣስታውስ/ሽ: ለፖሊስ መናገር ከፈራህ/ሽ ለሌላ የምታምነው/ኝው **ኣዋቂ ተናገር/ሪ።**





# የተመደበ ነርስ እና ጠቅላላ ሃኪም (GP)

## እነማን ናቸው

የተመደበ ነርስ (designated nurse) በማህበራዊ ኣገልግሎቶች የሚጠበቁት ልጆች **የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችን እና ጉዳዮች የሚረዳ** ነርስ ነው። **የጤና ፍላጎቶችህ/ሽ** መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ከማህበራዊ ሰራተኛህ/ሽ ጋር በመተባበር ይሰራሉ።


ጠቅላላ ሃኪም (GP) በተወሰነ **ኣካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች ኣጠቃላይ የህክምና ምክርና ህክምና የሚያቀርብ ሃኪም** ነው።

## ምን ይሰራሉ

የተመደበ ነርስ ሊመረምርህ/ሽ እና ማንኛውም የጤና ችግር ካለብህ/ሽ ሊፈትሽህ/ሽ ይፈልጋል። ይህም ቀዳሚ ምርመራ ("first assessment") ይባላል። ይህንን UK እንደደረስክ/ሽ ወዲያውኑ ሊያዘጋጁልህ/ሽ ይገባል። ምንም ኣይነት **የጤና ችግሮች** ወይም እንደ **በጣም የማዘን ስሜት ወይም የመተኛት ችግር** የመሳሰሉ ሌሎች ችግሮች ካሉብህ/ሽ **ጠቅላላ ሃኪምህን/ሽን በነፃ** ማየት ትችላለህ/ሽ። UK ውስጥ የጥርስ ወይም የአይን ሃኪምን ጨምሮ ለህክምና መክፈል **ኣያስፈልግህም/ሽም።**

ከነርስህ/ሽ ወይም ጠቅላላ ሃኪምህ/ሽ ጋር እየገጠሙህ/ሽ ስላሉ **ችግሮች ሃቀኛ መሆን** ኣትፍራ/ሪ። የተመደበልህ/ሽ ነርስ ከጠቅላላ ሃኪምህ/ሽ (GP) ጋር ለሚኖሩህ ቀጠሮዎች ኣብሮህ/ሽ የሚሆን **ኣስተርጓሚ** ሊይዝልህ/ሽ ይገባል።





# የቤት ቢሮ ጉዳይ ሰራተኛ

## እነማን ናቸው

የቤት ቢሮ ጉዳይ ሰራተኛ (Home Office case worker) በቃለ መጠይቅ ውስጥ ስለጥገኝነት **ይገባኛል ጥያቄህ/ሽ ጥያቄዎችን ይጠቅሃል/ሻል**፤ ኣንተ/ቺ ወይም ጠበቃህ/ሽ ስለይገባኛል ጥያቄህ/ሽ ያቀረባችሁትን **ማስረጃ ሁሉ ይመረምራል**፤ እና ይህን **መረጃ** መንግስት ካለው **መረጃ** እና **መምሪያ** ጋር ያነፃፅራል። ይህን ሁሉ **UK** ውስጥ **ለመቆየት** ምን ኣይነት **ፈቃድ** ሊሰጥህ/ሽ እንደሚችል ለመወሰን ይጠቀሙበታል።

## ምን ይሰራሉ

ለጉዳይ ሰራተኛው ስለጥገኝነት ይገባኛል ጥያቄህ/ሽ **የቻልከውን/ሽውን ያህል ብዙ መረጃ** ልትሰጠው/ጪው ያስፈልጋል። ጉዳይ ሰራተኛው ምቾት እንዲሰማህ/ሽ ሊያደርግ እና ጥያቄዎችን በመጠየቅና መልሶችህን/ሽን በማዳመጥ ምን እንደተፈጠረ እንድትረዳ/ጂ ሊያግዝህ/ሽ ይገባል።

ያጋጠመህን/ሽን ነገር ሁሉ ለጉዳይ ሰራተኛው ለመንገር **ኣትፍራ/ሪ** - ካልነገርካቸው/ሻቸው ሊያውቁ የሚችሉበት ምትሃታዊ መንገድ የላቸውም! ሁሌም እውነቱን መናግርህም/ሽም በጣም ኣስፈላጊ ነው እና መልሱን የማታውቀው/ቂው ወይም እርግጠኛ ያልሆንክ/ሽ ከሆነ ተናገር/ሪ። ይግባኝ **(appeal)** የመጠየቅ መብት ሊኖርህ/ሽ ስለሚችል **የጉዳይ ሰራተኛው ውሳኔ የመጨረሻ ኣይደለም።**

ወደ ብሄራዊ ጥቆማ ዘዴ **(National Referral Mechanism (NMR))** ተልከህ/ሽ ከሆነ በህገወጥ መንገድ ተዘዋውረሃል/ሻል ብለው ማሰብ ኣለማሰባቸውን የተለየ የቤት ቢሮ የጉዳይ ሰራተኛ ይወስናል። ይህ ውሳኔ የተለየ መሆን ኣለበት፣ ግን የእያንዳንዱ ውሳኔ መረጃ በተለያዩ ጉዳይ ሰራተኞች መካከል ሊጋራ ይችላል።






ኣሰልቺ ሊሆን በሚችል መልኩ ከተለያዩ ኣዋቂዎች ጋር ብዙ ቃለ መጠይቆች ውስጥ ልታልፍ ትችላለህ/ሽ። ትዕግስተኛ ሁን/ሁኚ።

አንድን ጥያቄ ለመመለስ ምንም ኣይነት ችግር ካለህ/ሽ፣ በጣም ከፈራህ/ሽ፣ ካፈርክ/ሽ፣ ደህና ካልሆንክ/ሽ፣ ወይም የማታስታውስ/ሽ ከሆነ ይህንን ማብራራት ኣለብህ/ሽ። “ኣሁን ስለዚህ ማውራት ኣልችልም” ማለት ይቻላል። ካልተናገክ/ሽ ቃለ መጠይቅ የሚያደርግልህ/ሽ ሰው ኣያውቅም፣ እና የነርሱ መረዳት ኣስፈላጊ ነው።



# ተገቢ ወይም ሃላፊነት የሚስወስድ ኣዋቂ

## እነማን ናቸው

ተገቢ ኣዋቂ (“appropriate adult”) ወይም ሃላፊነት የሚወስድ ኣዋቂ (“responsible adult”) ኣንድ ልጅ **ቃለ መጠይቅ በሚደረግለት ጊዜ መብቶቹንና ደህንነቱን የመጠበቅ** ሃላፊነት ያለው ሰው ነው።

## ምን ይሰራሉ

ኣንድ ተገቢ ኣዋቂ እንደ **የጥገኝነት ቃለ መጠይቅህ/ሽ፣ የእድሜ ምርመራ** (እድሜህን/ሽን የሚወስን መደበኛ ሂደት ነው) ወይም የፖሊስ ቃለ መጠይቅ ላሉ ቃለ መጠይቆች ኣብሮህ/ሽ ይሄዳል።

ራሱን የቻለ ድጋፍ ያቀርቡልሃል/ሻል፣ የቃለ መጠይቅ ኣቅራቢውን ትኩረት ኣንተ/ቺ ወደምትፈልጋቸው/ጊያቸው ነገሮች ሁሉ ያመጣልሃል/ሻል፣ እና ምን እየተካሄደ መሆኑን መረዳትህን/ሽንና መግባባት መቻልህን/ሽን ያረጋግጣል። ተገቢ ኣዋቂ **የማደጎ ወላጅ፣ ማህበራዊ ሰራተኛህ/ሽ፣ የስደተኛ ድጋፍ ድርጅት ሰራተኛ ወይም ሞግዚት** ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን የምታውቀው/ቂው እና የምታምነው/ኚው ሰው መሆን ኣለበት።



- ማንም ሰው ይቆጣኛል ወይም ባልጌ ነው/ ናት ብሎ ያስበኛል ብለህ/ሽ ኣትፍራ/ሪ
- ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ማደጎ ቤት ውስጥ ያሉ ደንቦችን ለመረዳት ከተቸገርክ/ሽ - ጠይቅ/ቂ



“ኣትፍራ/ሪ። እነዚህ ሰዎች እዚህ ያሉት ሊረዱህ/ሽ ነው። በጣም በቀላሉ ሊረዱህ/ሽ እንዲችሉ ከነሱ ጋር ግልፅ ለመሆን ሞክር/ሪ።”

“ምንም ነገር ቢሆን በጥንካሬ ቁም/ሚ። ወደኋላ ሳስታውሰው ምንም ኣይነት ድብርትና ጭንቀት ቢሆኑ የበዙት ተስፋ እየቆረጥኩ ስለነበረ ነው። ነገሮች ምንም መጥፎ ቢመስሉም የመጨረሻው ኣይደለም።”



- መረጃ ማጋራት እና እውነተኛ መሆን ኣስፈላጊ ነው
- የፈለከውን/ሽውን ያህል ጥያቄዎች ጠይቅ/ቂ እና የማትስማማበት/ማሚበት ነገር ካለ ተናገር/ሪ

# ጠበቃ

## እነማን ናቸው

ጠበቃ **ህጉን የሚያውቅና የሚረዳ** ሰው ነው። የፍልሰት ጠበቃ የቤት ቢሮው (Home Office) ባንተ/ቺ የጥገኝነት ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚጠቀምባቸውን ህግጋት **ያውቃል፣ ግን ለምሳሌ የወንጀል ህግ፣** የቤተሰብ ህግ፣ ወይም ማህበራዊ ኣገልግሎቶች ህግ የሚረዱ ሌሎች ኣይነት ጠበቃዎችም ኣሉ።

## ምን ይሰራሉ

ጠበቃው የሚሰራው ላንተ/ቺ ነው። ጠበቃው በጥገኝነት (asylum) ሂደት በኩል ስታልፍ/ፊ የሚያጋጥምህን/ሽን ነገር ፡ እና የባንተ/ቺ ሁኔታ ላይ ተለያዩ **ህጎች**ና **ሂደቶች** እንዴት እንደሚተገበሩ እንድትረዳ/ጂ ያግዝሻል። ይህንን ማድረግ እንዲችሉ ኣንተን/ቺን ምን እንዳጋጠመህ/ሽ ማወቅ ይፈልጋሉ። የምትናገረውን/ሪውን ማዳመጥ ኣለባቸው።

የጥገኝነት ይገባኛል ጥያቄህን/ሽን ሲያዘጋጁ ያጋጠመህን/ሽን ነገር ሁሉ ለመረዳት እንዲችሉ **ብዙ ጊዜ ሊያገኙህ/ሽ** ይፈልጋሉ። ጠበቃህን/ሽን ካልተረዳሃው/ሽው፣ ወይም ለማውራት ከፈራህ/ሽ ወይም ካፈርክ/ሽ ለሆነ ሰው መንገር ኣለብህ/ሽ። ከሌላ ጠብቃ ጋር መስራት ትችል/ይ ይሆናል።

ለጥገኝነት ይገባኛል ጥያቄህ/ሽ የሚጠቅሙ **የልምድህን/ሽን** ክፍሎች ለመለየት ጠበቃህ/ሽ ሊያግዝህ/ሽ ይገባል። በሁሉም ከፍልሰት ሃላፊዎችና ከፖሊስ ጋር ለምታደርጋቸው/ጊያቸው መደበኛ ቃለ መጠይቆች ኣብረውህ/ሽ ሊሆኑና **መረጃ በጊዜው ማቅረብህን/ሽን** ሊያረጋግጡ ይገባል።

ጠበቃህ/ሽ በጥገኝነት ማመልከቻህ/ሽ ላይ ለመስራት **ገንዘብ ሊጠይቅህ/ሽ ኣይገባም።** ጉዳይህን/ሽን ለማዘጋጀት ባንተ/ቺ ምትክ “ህጋዊ እገዛ” ተብሎ የሚጠራ ገንዘብ ከመንግስት ድርጅት መጠየቅ ይችላሉ፣ ይህ ማለት ግን ለመንግስት ይሰራሉ ማለት ኣይደለም።



